# የACPS Express 8/20/2021: ለ'Back to School' በቅርብ-ጊዜ የወጣ አዲስና ማስተካከያዎች (Updates)

## የጠቅላይ ስራ አስኪያጁ የቪዲዮ አዲስና ማስተካከያ (Update) መልዕክት፣ ለቤተሰቦች እና ሠራተኞች

ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ፣ ዶ/ር ግሪገሪ ሲ. ሃችሂንግስ (Dr. Gregory C. Hutchings, Jr)፤ ወደ አስደሳቹ አዲስ የትምህርት ዓመት፣ ተማሪዎቻችንን እና ሠራተኞችን እንኳን ደህና መጣችሁ ይላሉ!

[ቪዲዮ: የጠቅላይ ስራ አስኪያጁ የቪዲዮ አዲስና ማስተካከያ (Update) መልዕክት፣ ለቤተሰቦች እና ሠራተኞች]




## የአሌክሳንድሪያ ከተማ መንግስት እና የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፤ ለተቀጣሪ-ሠራተኞች የCOVID-19 ክትባትን እና ምርመራን መስፈርቶች ለማስፈጸም ጥምረት ፈጥረዋል

የአሌክሳንድሪያ ከተማ እና የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ACPS)፤ የCOVID-19 ክትባትን እና ምርመራን መስፈርቶችን ለሁሉም የከተማው መንግስት እና ለACPS ትምህርት ቤት ሠራተኞች ለማስፈጸም በአንድነት ጥምረትን ፈጥረዋል። በአሁኑ-ጊዜ እየተስፋፋ ባለው የCOVID-19 ታማሚዎች በጨመረበት ወቅት፣ ይህ የጥምረት-እርምጃ፣ በአሌክሳንድርያ እና በግዛቱ በመስፋፋት ላይ ያለውን ቫይረስ ለመግታት አስፈላጊ በሆነው እርምጃ ላይ ተጨማሪ በመሆን፤ ከአሌክሳንድርያ ጤና መምሪያ (Alexandria Health Department (AHD) ከተሰጠው መመሪያ ጋር አብሮ የሚሄድ ይሆናል።

ከፍተኛ የመዛመት አቅም ባለው የ'ዴልታ-ቫሪየንት (delta variant)' ባስከተለው፣ የክልሉ የCOVID-19 ህመም ያለባቸው ቁጥር መጨመር ምክንያት፤ አሌክሳንድርያ በዚህ ሣምንት፣ በ[ከፍተኛ የማህበረሰብ ስርጭት (high community transmission)] ምድብ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention) እና የቨርጅኒያ የጤና መምሪያ፤ እንደገለጹት - የCOVID-19 ክትባት፣ አሁንም ቢሆን በጣም የሚሰራ እንደሆነ እና ጉልህ በሆነ መንገድ ስርጭቱን፣ ህመምን፣ በሆስፒታል ውስጥ መግባትን እና ሞትን እንደሚቀንስ መግለፃቸውን ቀጥለዋል።

“ባለፈው አንድ ወር-ከግማሽ በላይ፣ አሌክሳንድርያ በተደጋጋሚ እየጨመረ የመጣ በሽታው ያለባቸው ህሙማን ቁጥር መኖሩን እና ከኤፕሪል-አጋማሽ (mid-Apri) በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በከፍተኛ የማህበረሰብ ስርጭት ምድብ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። የሕዝብ ተቋማት ለነዋሪዎች፤ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ስርጭትን የቀነሰ፣ እና ለቫይረሱ መጋለጥን እና ከዚህ ቀደም የገጠመንን ተሞክሮ እንዳይኖር ለማድረግ፤ የሚቻለንን እርምጃዎች በሙሉ መውሰድ አለብን፣” ብለዋል የከተማው አስተዳዳር፣ ማርክ ጂንክስ (Mark Jinks)። “እንደ ዋነኛ የተቀጣሪ-ሠራተኞች ቁጥር ብዛት አንፃር፤ ከተማው እና የትምህርት ቤት ክፍሉ፣ ይህን የወረርሽኝ የጤና ሁኔታን መፍትሄ ለመስጠት በጋራ ትብብር እንሰራለን። ይህ አዲሱ የችግር-ቅነሳ እርምጃ፣ አሁን-ባለው ላይ ተጨማሪ ደረጃ ያለው የመከላከያ መስፈቶችን፣ የክትባት ሁኔታቸው ምንም-ሆነ-ምን፣ ለሠራተኞች እና ለጎብኚ-እንግዶች በመጨመር፤ በከተማው እና በACPS ተቋማት ውስጥ የፊት መሸፈኛ ማኮችን (masks)ን በCDC በሚመከረው መሠረት እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።

የከተማው እና የACPS ቅጥር-ሠራተኞች፤ የክትባት ሰነድን ለሚመለከተው ኤጀንሲያቸው እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ያልተከተቡ ሁሉም ተቀጣሪ-ሠራተኞች ወይም የክትባት ሁኔታቸውን መግለጽ የማይፈልጉ፤ ያለውን-ስርጭቱን በስራ-ሃይሉ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ለመቀነስ፣ በየሣምንቱ የCOVID-19 ምርመራን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ። ምርመራው፣ ለተቀጣሪ-ሠራተኞች ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ክፍያ አይጠይቅም። በመጪው ሣምንት ለከተማው እና ለACPS ሠራተኞች፣ ዝርዝሮችን እናጋራለን።

በዚህ ኦገስት (August) 19 ቀን፣ በልዩ ሁኔታ በተጠራው የቦርድ ስብሰባ ላይ፣  ሁሉም የACPS ሠራተኞች በሣምንታዊ የCOVID-19 ምርመራ እና የክትባት ሁኔታቸው መጠናቀቁን በፈቃደኝነት ሪፖርት ማድረግን፤ ጠቅላይ ስራ አስኪያጅ፣ ዶ/ር ግሪገሪ ሲ. ሃችሂንግስ (Dr. Gregory C. Hutchings, Jr) ያቀረቡን ሃሳብ የትምህርት ቤቱ ቦርድ፣ በአንድ-ድምጽ አጽድቀዋል። “ይህ፣ በአሁኑ-ጊዜ ላለን የጤና እና የደህንነት ቅነሳ እርምጃዎች፣ ወሳኝ የሆነ መሣሪያ ነው። በትምህርት ቤታችን ተቋማት ውስጥ የቫይረሱን ስርጭት ቅነሳን ለማገዝ እና ማህበረሰባችንን በአጠቃላይ ለመጠበቅ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን ለማጠንከር፣ ቀልጣፋ እርምጃን የምንወስድበት ነው፣” ብለዋል፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የቦርድ ሊቀመንበር የሆኑት ሜጋን ኤል. አልደርተን (Meagan L. Alderton)።

የአሌክሳንድርያ፣ ዕድሜያቸው 12 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ [የክትባት መጠን] አጠቃላይ ምልከታው፣ በአሁኑ-ጊዜ 60.4% ነው። የCOVID-19 ክትባቶች፣ ችግር የማይፈጥሩ፣ ውጤታማ፣ ነፃ እና ዕድሜአቸው 12 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ በአቾኋይ ክትባቱን መውሰድ የሚያስፈልጋቸው ነው። AHD እና ክትባት ሰጪ ተባባሪዎቹ፤ ክፍት የሆነ የክትባት መስጠትን የጊዜ-ሰሌዳን እና ካለቀጠሮ የመምጣት አማራጭን በአሁኑ-ጊዜ ይሰጣል።

ክትባትዎን ዛሬውኑ ለማግኘት ወይም ለበለጠ መረጃ፣ alexandriava.gov/Vaccines ላይ ይጎብኙ።

# ለ‘Back to School’ በቅርብ-ጊዜ የወጣ አዲስና ማስተካከያዎች (Updates)




ከK-12 ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እንደገና ወደ ትምህርት የሚመለሱበትን፣ ኦገስት (Aug.) 24 ቀንን፣ በጉጉት እንጠባበቃለን። ለpre-K፣ የመጀመሪያ ቀን የሚሆነው ኦገስት (Aug.) 26 ቀን ነው። ስለ ተማሪዎች እና አስተማሪዎች፤ ተገልሎ መቆያ (Quarantine) ሂደት፣ የ‘back to school’ ቅጾችም፣ ሃገር-አቀፍ ነፃ ምግቦች፣ አውቶቡስ መጓጓዣ እና ሌሎች ተጨማሪዎችን ለማግኘት ብቁነት በተመለከተ የበለጠ ይወቁ።

## ለተማሪዎች እና አስተማሪዎች፤ ተገልሎ መቆያ (Quarantine) ሂደት

ተከስቶ በነበረ የCOVID-19 መጋለጥ ምክንያት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተማሪዎች ተገልሎ መቆየት (quarantine) ሊያስፈልግ በሚችልበት ሁኔታ ላይ፤ ACPS ተገልለው ለሚገኙ ተማሪዎች፣ የቀጥታ ስርጭት በሆነ የትምህርት አሰጣጥን በመጠቀም እገዛ ያደርጋል። የቀጥታ-ስርጭቱ፣ ተማሪዎች አስተማሪዎቻቸው በአካል-በተገኙበት የመማሪያ ክፍል ሆነው በጊዜ-የሚሰጡትን ትምህርት መመልከት ይችላሉ። ተማሪዎች፣ የክፍል/የቤት ስራዎቻቸውን (assignments) ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው እና የአስተማሪ የቢሮ ሰዓታትን ውስጥ ይማራሉ።

አስተማሪው ተገልሎ መቆየት (quarantine) ማድረግ በሚያስፈልገው ጊዜ፤  ከተተኪ አስተማሪው ጋር በክፍል ውስጥ፣ መደበኛ አስተማሪው ደግሞ በርቀት (virtually) ክፍለጊዜውን በማስተማር ተማሪዎች ይማራሉ።

ተገልሎ በመቆያው (quarantine) ጊዜ፣ ይህ ሁኔታ በሚከሰት ጊዜ መመሪያው ለተማሪዎች ይሰጣል። በርካታ ሁኔታዎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሲከሰቱ፣ ዝርዝር ሁኔታዎችን ከዝርዝር መግለጫው ላይ በ‘Quarantine Process for Students and Teachers’ ይመልከቱ።

ለማስታወስ ያህል፤ ተማሪዎች እና ሠራተኞች በማንኛውም ምክንያት ህመም ከተሰማቸው ወደትምህርት ቤት ወይም ወደስራ ቦታቸው መምጣት የለባቸውም። ሕመም ሲሰማችሁ በመኖሪያ ቤታችሁ ውስጥ በመቆየት፣ እባካችሁን በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ ሁሉም በደህንነት እና በጤና ለመጠበቅ እርዱን።

## ለሁሉም ተማሪዎች፣ የምሣ ሂደት

ወደ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር በምንመለስበት ጊዜ፣ ACPS ቁርስ እና ምሣ ካለምንም ክፍያ ያቀርባል። ACPS

በምሣ ሂደቱ ውስጥ፣ የጤና እና የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን በማካተት፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ውስጥ፣ ሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ለምሣ በተመደበው ጊዜ ውስጥ ደህንነታቸው መጠበቁም ለማረጋገጥ ይሰራል።

በሁሉም የትምህርት ቤት ካፊቴሪያዎች የአየር ማጣሪያ እንዲሰሩ ይደረጋል፣ እና የካፊቴሪያ ቦታዎች በመደበኛነት እና ከስር-መሠረቱ የሚጸዱ እና ከብክለት ማጽጃዎችን (sanitizing solution) በመቀጠም ይጸዳል። በምሣ-ሰዓቱ ወቅት፣ ተማሪዎች እንዲመዘገቡ (sign in እንዲያደርጉ)፣ እጃቸውን እንዲታጠቡ፣ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን በካፊቴሪያ ውስጥ ለመጠበቅ በተመደቡበት ቦታዎች እንዲቀመጡ፣ እና በማይበሉበት ጊዜ የፊት መሸፈኛ ማስኮች (masks)ን እንዲጠቀሙ ይጠየቃሉ።

ትምህርት ቤቶች፣ በካፊቴሪያዎች ውስጥ ለምሣ-ሰዓት የሚኖራቸውን የመያዝ አቅም ይወስናሉ። በመጀመሪያ ደረጃ እና በመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ደረጃዎች ውስጥ፣ የጊዜ-ሰሌዳ በየክፍል ደረጃ በተያዘበት እና/ወይም የክፍል ሰዓት ጊዜያቸው ውስጥ ተማሪዎች ይበላሉ። ተማሪዎች በተለመደው ካፊቴሪያ ውስጥ ይበላሉ፣ ሆኖም አንዳንዶች ምናልባት በየክፍላቸው ሊበሉ ይችላሉ። በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ባለው ደረጃ፣ ሁሉም ተማሪዎች በአንድ-ዓይነት ሰዓት የሚበሉ እና በአጠቃላይ በህንጻው የት ምሣ መብላት እንደሚፈልጉ በመወሰን፤ በተለመደው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የካፊቴሪያ አቀማመጥ ላይ የመጨናነቅን ጭንቀትን ያስወግዳል። በቀድሞ ዓመታት ሲደረጉ እንደነበረው፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ እደጅ-የውጪ ቦታዎችን ለምሣ መጠቀማቸውን ይቀጥላሉ።

ይህ የምሣ ሂደት፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የጤና እና የደህንነት ጥበቃ ፕሮቶኮሎችን ለማስፈጸምና ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን መቀነስ እና በንክኪ ምክንያት ሊኖር የሚችል መጠጋጋትን ይቀንሳል። ይህ በእንዲህ እያለ፣ ተማሪዎች የምሣ-ሰዓት ጊዜያቸውን በካፊቴሪያ ውስጥ ወይም በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ደህንነቱ በተጠበቀ እና አስፈላጊ የሆነውን የእርስ-በእርስ ግንኙነትን በመጠበቅ ይካሄዳል።

## ለ2021-22 ‘Back to School’ ቅጾች

የ‘Back to school’ ቅጾችን፣ በኦንላይን በ‘PowerSchool Parent Access’ አማካኝነት የሚገኝ ይሆናል። የACPS ዓላማ፤ ሁሉም ቤተሰቦች፣ ‘PowerSchool Parent Access’ን፤ እንደ-የተማሪያቸው ማገናኘ መሣሪያ ማድረጊያነት እና ከትምህርት ቤት ክፍሉ ጋር አጋርነትን እንደመፍጠሪያ ለመጠቀም ኃይል መስጠት ነው።

እባክዎን የ‘Back to School’ ቅጾችን* እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 15 ቀን 2021 ድረስ አጠናቁ፤ የሚከተለውን አዲስና ማሻሻያዎች (Updates)ን ለማድረግ:

- የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎችን እንድታገኙ፤ የምትገኙበትን የአድራሻ-መረጃን አቅርቡ
- ለተማሪዎ፤ በአደጋ-ጊዜ መገኘት የሚችሉ ሰዎች አድራሻዎች
- የልጅዎን የጤና መረጃ አቅርቡ
- ለመውጣት (opt-out ለማድረግ) ያላችሁን ምርጫ አሳውቁ

በACPS ውስጥ፣ ከአንድ በላይ ልጅ ካለዎት፣ እባክዎን ለእያንዳንዱ ልጅ፣ ቅጾቹን በመሙላት ያጠናቅቁ።

የታተሙ ጥራዞች፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች፤ ተመራጭ-ቋንቋቸው እነዚህ ቋንቋዎች እንደሆኑ ለዘረዘሩ፣ የተማሪዎች-ቤተሰቦች፤ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው፣ ባዶ ያልተሞሉ ቅጾችን፤ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚጠይቁ ቤተሰቦች ለመስጠትም አዘጋጅተናል።

የ‘Back to School’ ቅጾችን ሞልቶ ማጠናቀቂያ የት ዕዛዝ መመሪያዎችን ተመልከቱ።.

## የጤና እና የክትባቶች (Immunizations) ቅጾች

ሁሉም የጤና ቅጾች እና ክትባቶች (Immunizations)፣ ወቅቱን የጠበቁ መሆናቸውን ቤተሰቦች ማረጋገጣቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

- የ ‘Medical Forms and Policies’ ላይ ምልከታ አድርጉ እና እንደ አስፈላጊነቱ ቅጾቹን አስገቡ።

- ልጅዎ፣ በሁሉም ክትባቶች እና/ወይም በቨርጂኒያ የጤና መምሪያ በሚጠየቀው መሠረት አካላዊ ምርመራን (physicals) ወቅቱን-የጠበቀ መሆኑን አረጋግጡ። እነዚህ፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) ወይም በርቀት (virtual) ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልግ ነው።
- እንደ-ተቻለ እና ተገቢ-እስከሆኑ ድረስ፣ ሁሉም የሚሰጡ መድኀኒቶች፣ በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች ከትምህርት-ጊዜው ውጪ በሆኑ ሰዓታት መከናወን አለባቸው። መድኀኒቶች (medications) በትምህርት ቤት ሰዓቱ መከናወን ካለበት፣ እባክዎን ይህን ቅጽ፣ 'Authorization to Administer Medication Form (PDF)' ይሙሉ።

## ሁሉም የ'ACPS' ተማሪዎች፣ ለነፃ ምግቦች ብቁ ናቸው፤ ለሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞች ማመልከቻዎች ያስፈልጋሉ

ሁሉም ተማሪዎች፣ ትምህርት ከሚጀመርበት የመጀመሪያ-ቀን ጀምሮ እስከ ጁን (June) 30 ቀን 2022 ድረስ፤ በACPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ካለምንም ክፍያ ምግቦችን ለማግኘት ብቁ ናቸው። የACPS ቤተሰቦች፣ በወረርሽኝ የኤሌክትሮኒክ ጥቅማ-ጥቅም ማስተላለፊያ (Pandemic Electronic Benefits Transfer (P-EBT) ፕሮግራም ውስጥ መግባት ከፈለጉ፣ እንዲሁም ለሌሎች ጥቅማ-ጥቅሞች ብቁ ሆኖ ለመገኘት፤ ለነፃ ምግቦች በተቻለ ፍጥነት ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ ይበረታታሉ። የ'P-EBT ጥቅማ-ጥቅም፣ አሁን የሚገኘውን የአመጋገብ ፕሮግራሞችን ለማገዝ፣ በCOVID-19 ወረርሽኝ ወቅት፣ አነስተኛ-ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የሚሰጥ ነው።

የማመልከቻ ቅጾቹ፣ ለሁሉም ተማሪዎች ወደየቤታቸው የተላከ እና በተጨማሪም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዋናው ቢሮ ውስጥ መገኘት ይችላል። ወይም፣ እዚህ ነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) ማመልከቻን ዳውሎድ (download)ማድረግ ይቻላል። ሆኖም፤ ፈጣን-የሆነ ውጤቶችን እንድታገኙ፤ በኦንላይን እንድታመለክቱ፣ እናበረታታለን። በየአንዳንዱ የትምህርት ዓመት አዲስ ማመልከቻ የሚያስፈልግበት ምክንያት፤ ለሌሎች ፕሮግራሞች የሚሰጠው የትምህርት ቤት የገንዘብ-እርዳታ እና ብቁነት፣ በተጠናቀቀው የምግብ ማመልከቻዎች ላይ መሠረት ስለሚያደርጉ ነው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የACPS ነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) ድህረ-ገጽን ይጎብኙ።

## የአውቶቡስ መጓጓዣ

የACPS ቤተሰቦች፣ የተማሪዎቻቸውን የአውቶቡስ መጓጓዣ መረጃን በኢሜል አማካኝነት በኦገስት (Aug.)18 ቀን አግኝተዋል። ይህ መረጃ፣ በPowerSchool Parent Access ውስጥም የሚገኝ ይሆናል። የCOVID-19 ቅነሳ ጥረቶች በሚካሄዱበት ወቅት፤ ሁሉም ተማሪዎች፣ የፊት መሸፈኛ ማስክ (mask)ን በማንኛውም የACPS ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ ማድረግ እንዳለባቸው እባክዎን ያስታውሱ። ተማሪዎች በአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታዎች ላይ፣ ከሚወሰዱበት የጊዜ-ሰሌዳ ጊዜ 10 ደቂቃዎችን ቀደም ብለው እንዲገኙ ይጠየቃሉ።

ተማሪዎች ወደ አውቶቡስ ከመግባታቸው በፊት፤ ቤተሰቦቻቸው የዕለታዊ የህመም ምልክትን መመልከቻ (Checklist)ን ማጠናቀቅ አለባቸው። ሁሉም ተማሪዎች፣ ወደ አውቶቡስ ከመግባታቸው በፊት የፊት መሸፈኛ (mask) አድርገው እና ከኋላ ወደፊት እንዲገቡ የሚደረግ ሲሆን፣ ይህም ተማሪዎች ቦታ ለማግኘት እርስ በርስ ከመተላለፍ ለመጠበቅ፣ የመዋዕለሕጻናት ተማሪዎች ወደፊት በሚገኘው ቦታ መቀመጣቸውን በመጠበቅ ነው። ሁሉም ሹፌሮች እና ተቆጣጣሪዎችም፣ የፊት መሸፈኛ ማስኮችን (masks) ማድረግ አለባቸው። ንክኪ ያላቸውን መከታተል (Contact tracing) ለመከታተል እንዲረዳ፣ ተማሪዎች ከዚያው አንድ ተማሪ ጎን ሁልጊዜ እንዲቀመጡ እንጠይቃለን። ለእያንዳንዱ ቀን የተሳፋሪዎችን ማንነት ለማወቅ፣ የስም ዝርዝር በሹፌሩ ይያዛል። ሹፌሮች እንደአስፈላጊነቱ መስኮቶችን ይከፍታሉ (መጥፎ የአየር ሁኔታ በሚኖር ጊዜ/ሞቃት አየር ሲኖር አይመከርም)።

በትምህርት ቤት በየቀኑ በሚመጡ-ጊዜ የተማሪዎችን የሰውነት ሙቀትን መመርመር (temperature scanning) ያሉትን፣ የጤና እና የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን ትምህርት ቤቶች ማስፈጸም እንዲችሉ፣ የሁሉንም ትዕግስት እንጠይቃለን። ይህን ሂደት ተማሪዎች እና ሠራተኞች እስከሚለምዱት ድረስ መዘግየት ሊታይ ይችል ይሆናል። የሰውነት ሙቀት መመርመር (temperature

scanning) እስከሚከናወን ድረስ በአውቶቡሶች ውስጥ ተሰልፈው ተማሪዎች መቆየት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣ ይህ ተማሪዎችን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት የመውሰጃ (pickup) እና የማውረጃ (delivery) ጊዜ ላይ ተጽዕኖ ያደርሳል። ተማሪዎችን የማውረጃ (drop-off) ጊዜ - ጠዋት ጠዋት ላይ፣ የጥቂት ደቂቃዎች መዘግየት ሊኖር ይችል ይሆናል፤ እና በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ሣምንት ወቅት የተለመደ ተደጋጋሚ ሂደቱን (routine) እስከምንፈጥር ድረስ፣ ሁኔታዎቹን ስለተገነዘባችሁ እና ስለትዕግስታችሁ እናመሰግናችኋለን።

## በትምህርት ቤት ተቋማት ውስጥ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (Volunteers) እና ጎብኚ-እንግዶች

ACPS በቦታው ካስቀመጣቸው፣ እንደ-አንዱ የጤና ቀውስ ቅነሳ እርጃዎች በመሆን ያስቀመጠው፤ የጎብኚ-እንግዶችን ቁጥር በትምህርት ቤት ተቋማት ውስጥ መወሰን ነው። ቤተሰቦች፣ ከትምህርት ቤቶቻቸው ውጪ ተማሪዎችን በማውረጃው ቦታ (drop off) እንዲያወርዷቸው ይጠየቃሉ። የጎብኚ-እንግዶች ቁጥር ውሱን ነው። አስፈላጊ-በመሆናቸው ፍቃድ-ያገኙ ሁሉም እንግዶች፣ በተቀመጠው የደህንነት-ጥበቃ፣ መከላከልና-ቅነሳ ስልቶችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

አስፈላጊ-የሆኑ ጎብኙዎች፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers) እና እንቅስቃሴዎች በሚከተሉት-ሁኔታ ውስን ይሆናሉ:

- በአካል ተገኝቶ (in-person) ተማሪዎች እገዛዎችን ለማቅረብ እርዳታ የሚሰጡ ግለሰቦች፤ የከተማ እና የትብብር ፕሮግራሞችን ለማከናወን ጨምሮ
- የACPS ክንውኖችን እና የጥገና-ስራዎችን የሚያግዙ/የሚያከናውኑ ግለሰቦች፤ እና
- በትምህርት ቀኑ ወቅት፣ ሕመም የተሰማቸው ተማሪዎችን ለመውሰድ የሚመጡ ግለሰቦች

አስፈላጊ-የሆኑ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers)፣ ጎብኚ-እንግዶች፣ እና ኮንትራክት ሠራተኞች ተብለው ለተለዩት፣ ተጨማሪ መመሪያ ወደፊት ይገለፃል።

በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ስለጤና እና የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች፣
ተጨማሪ ዝርዝሮች እና አዲስና ማስተካከያዎች (updates)ን፣ በHealth and Safety Guidance Overview webpage ላይ ይጎብኙ።

## በACPS ውስጥ፤ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት

በተማሪዎቻችን ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ያነጣጠሩትን፣ የCOVID-19 እና በስልታዊ ዘረኝነት (systemic racism) የሁለትዮሽ ወረርሽኞች፤ ACPS የስርዓተ ትምህርት ትኩረቱን በተማሪ የማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) ፍላጎቶችን የመጠበቅ አስፈላጊነትን እውቅና ይሰጣል። ይህን በአዕምሮአችን በማስቀመጥ፣ ተማሪዎች የSEAL ትምህርቶችን እንደ ዕለታዊ ልምዶች በማድረግ እንዲያገኙ ያደርጋል። እነዚህ ትምህርቶች፤ ተማሪዎች ስሜቶቻቸውን በመፈተሽ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ፣ ከእኩዮቻቸው ጋር እና ከትምህት ቤት ሠራተኞች ጋር ግንኙነትን ለመገንባት፣ እና ተጨማሪ የቀለም ትምህርት እና የስራ መስክ ርዕሶች ላይ ዳሰሳ እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል። ተጨማሪ የSEAL እገዛዎች የሚያስፈልጓቸው ተማሪዎች፤ በትምህርት ቤቱ ባለብዙ-ደረጃዎች የስርዓተ እገዛ (Multi-Tiered System of Support (MTSS) ሂደት አማካኝነት የሚለዩ ሲሆን፣ እንዲሁም ተጨማሪ የሆነ ጣልቃ-ገብነቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል።

የሁሉም ተማሪዎች የስሜታዊ እና ማህበራዊ ጤናማነት፣ ከፍተኛ ቀደምትነት በACPS ውስጥ ይሰጠዋል። የተማሪ የእገዛ ቡድን (Student Support Team) ሠራተኛ፤ የትምህርት ቤት ካውንስለሮችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶች፣ የትምህርት ቤት የስነልቦና ሃኪሞች፣ እና የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኛ (social workers)፤ በመደበኛው የትምህርት ቤት ሰዓታት ውስጥ የሚገኙ ይሆናሉ። የቀለም ትምህርቶችን እና ክፍለጊዜዎችን፣ ስሜታዊ-ስጋቶችን፣ እና ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ (post-secondary) እቅድ አወጣጥን በተመለከተ፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ላሏቸው ጥያቄዎች፣ እርዳታ ለመስጠት ዝግጁ ነን። የተማሪ አገልግሎቶች መምሪያ ( Department of Student Services) እና የፍትሃዊ እኩልነት የሠራተኛ አባላት፤ በዚህ ጊዜ በተጨማሪ በሚከተለው አድራሻ መገኘት ይችላሉ:

- መልዕክት (voicemail) በ703-446-8034 ተዉልን።

- ኢሜል: student_services@acps.k12.va.us

## ለሣምንቱ፣ በተጨማሪነት የምንነግራችሁ ነገሮች

- Upcoming COVID-19 Vaccination Clinics from AHD
- ACPS Special Education Newsletter (PDF)
- የቲታን አትሌቲክ ቡስተር ፈቃድ (Titan Athletic Booster Pass)ን መግዛት
- የቲታኖች የአትሌቲክ አፕ (Titans Athletic App)ን ዳውንሎድ (Download) ማድረግ

### የቲታን አትሌቲክ ቡስተር ፈቃድ (Titan Athletic Booster Pass)ን መግዛት

በዚህ ዓመት የACHS የቲታኖች አትሌቲክ ቡስተር ክለብ (Titans Athletic Booster Club)፤ ለማንኛውም መደበኛ የሲዝኑ የአትሌቲክ ዝግጅት የሚያገለግለውን፣ የሲዝኑን የዝግጅት ማለፊያ ፈቃዶችን ስፖርሰር ያደርጋል። የተማሪዎች የሲዝኑ የማለፊያ ፈቃዶች (season passes) $35 ሲሆን፣ የግለሰብ የሲዝን የማለፊያ ፈቃዶች $75፣ እንዲሁም የቤተሰብ የሲዝን ማለፊያ የሆነው ደግሞ - አራት ፈቃዶችን የሚያካትተው (ሁለት የአዋቂዎች እና ሁለት ተማሪዎች) $175፣ ይሆናል። እነዚህ የፈቃድ ማለፊያዎች፣ ወደ ማንኛውም መደበኛ-የሲዝን የስፖርት ዝግጅት ውስጥ፣ ለአጠቃላይ የትምህርት ዓመቱ መግቢያ ሲሆኑ፣ ነገር ግን ወደ ዲስትሪክት፣ ግዛት ወይም ስቴት የጨዋታ ግጥሚያዎች መግቢያነት ሆነው አይካተቱም። እነዚህን ማለፊያ ፈቃዶች መግዛትዎ፣ ለአትሌቲክ ቡስተር ክለብ (Athletic Booster Club) አባልነትን ያስገኛል።

የ'Titans GoFan' ድህረ-ገጽ websiteን በመጎብኘት፣ የማለፊያ ፈቃዶችዎን ለመግዛት እና በሁሉም ስፖርቶች ቲታኖችን (Titans) ለመደገፍ ይምጡ!

### የቲታኖች የአትሌቲክ አፕ (Titans Athletic App)ን ዳውንሎድ (Download) ማድረግ

የቲታን አትሌቲክ መምሪያ፣ የሞባይል አፕን ለቲንታን ደጋፊዎች (Titan fans) ያስተዋውቃል። የ"ቲታኖች አትሌቲክስ (itans Athletics)" አፕ (app)፤ የአትሌቲክ መረጃን፣ የሞባይል ቲኬት-መግዣ፣ እና በቅርብ-ጊዜ የወጡ የቲታን ዜናዎችን ለማህበረሰቡ ማሳወቂያ ጥቆማ መስጫን (push notifications) የያዘ ነው። ይህ አፕ (app)፤ በጨዋታው-ቀን ለሚኖሩ - የጊዜ-ሰሌዳዎችን፣ የጨዋታ ውጤቶችን፣ የቡድን መረጃ፣ እና የማህበራዊ አስተያየቶችን አካቶ የሚይዝ አንድ-ቦታ ሆኖ ለደጋፊዎች ያገለግላል። ይህ አፕ (app)፤ አዲስ በማስታወቂያ የሚቀርቡ ነገሮችን ለደጋፊዎች፣ ከበርካታ የACHS ስፖንሰሮች ያቀርባል።

ደጋፊዎች፤ ከሁለቱም ከአፕል አፕ ስቶር (Apple App Store) እና ከጉግል ፕሌ (Google Play)፣ የቲታኖች የአትሌቲክ አፕ (Titans Athletic App)ን ዳውንሎድ (Download) ማድረግ ይችላሉ።

---

**ጥያቄዎች፣ ስጋቶች ወይም አስተያየቶች አሏችሁ? ያነጋግሩን።**